# በሙስሊሙ ስም የተሰናዳ የፖለቲካ ጨዋታ

**ሸሪፋ ከድር 1/13/13**

የተገኘውን ነገር ያለምንም የጥሬ ሃቅ ዳሰሳ ብሎም በአንድ ወገን ኢ-ሙያዊ ዝማሜ እንዳለ ለህዝብ በማቅረብ የሚታወቀው ፍትህ ጋዜጣ በራሱ ጊዜ ከተዘጋ በኋላ፤ እንደ አዲስ "አዲስ ታይምስ" በሚል የጨለማ መዘመሪያ መፅሔት ላይ በመሰባሰብ እዚህ ሀገር ውስጥ አንዳችም በጎ ነገር የሌለ በማስመሰል "በተልዕኮ" የሚሰሩት የያኔዎቹ የጋዜጣው ጋዜጠኛ መሳይ ፖለቲከኞች ዛሬም "አሸሸ ገዳሜ፣ መቼ ነው ቅዳሜ" እያሉ በየ15 ቀኑ ዳንኪራ እየረገጡ ነው።

የዳንኪራቸው "ዋነኛው ዲጄ" /ግንባር ቀደም አስጨፋሪ/ አቶ ተመስገን ደሳለኝ በተውሸለሸለ እንዲሁም የራሳቸውን ጨምሮ በተለያዩ ፎቶዎች እየነገዱ በአደናቁር ስልተ-ምት ቅኝቱን ስለሚመሩት አብዛኛዎቹ የጨለማው መንገድ የፅሑፍ ተውረግራጊዎች ከአሉባልታና ከግልብ ስሜት በዘለለ ጠብ የሚል ሃቅ ሲያስነብቡን አይስተዋልም።

የአቶ ተመስገን ደሳለኝ ግልገል ተውረግራጊው ኃይለ መስቀል በሸዋምየለህም ቢሆኑ የፈረንጆችን አንዳንድ ጥናታዊ ፅሑፍ እንደ ማያወላዳ ትክክለኛ ማስረጃ በመቁጠር እንግሊዘኛን ወደ አማርኛ እየተረጎሙ የሰውን ሃሳብ እየደገፉ የራሳቸውን አሊያም አቶ ተመስገን የሚያገለግሉትን ርዕዮተ-ዓለምንና ግለሰቦችን በመደገፍ የተሰለፉ ግለሰብ ናቸው።

ታዲያ የፈረንጆችን ጥቅስ አሊያም የአክራሪ ሙስሊሞችንና ድብቅ ወኪሎቻቸውን የብዕር ጨዋታ ከየጎራው እየለቃቀሙ በመተርጎም የራሳቸውን ወይም ያዘዟቸውን ሃይሎች የፖለቲካ ፍላጎት ግብ ለመምታት የሚውተረተሩት እኚሁ ግለሰብ፤ ሰሞኑን በአታሞ መደለቂያቸው አዲስ ታይምስ መፅሔት የታህሳስ 2005 ዓ.ም ዕትም ላይ አንድ ርዕሰ-ጉዳይን ይዘው ብቅ ብለዋል፡፡

በእርግጥ ጉዳዩን ግለሰቡ እንደ አዲስ ይዘውት መጡ እንጂ፣ እኛ ሙስሊሞች ደግመን ደጋግመን የተወያየንበትና መፍትሔም ያበጀንለት፣ ያለቀቀና የደቀቀ ነገር ነው፡፡ ፀሐፊው ወይም ተርጓሚው የባለ ሶስት ገጽ አቧራው ጨሰ ዘገባቸውን "የሙስሊሙ መንገድ" በሚል ርዕስ ቋጥረውታል፤ የሙስሊሙ ወጣቶች መዝሙር ያሉትን "አሽ ሸዓብ ዩሪድ ተቅይሩል መጅሊስ"ን ደግሞ በንዑስ ርዕስነት መርጠዋል፡፡

እንደ ሙስሊምነቴ ለግለሰቡ ምናልባት ምላሽ ትሆንልኝ ዘንድ ይህችን ጽሁፍ ለመጫር ያነሳሳኝም ይኸው አቶ ኃይለመስቀል በሸዋምየለህ የሙስሊም ወጣቶች መዝሙር ያሉት ጉዳይ ኮርኩሮኝ ነው፡፡ እናም ዕውን "አሽ ሸዓብ ዩሪድ ተቀይሩል መጅሊስ" የኢትዮጵያ ሙስሊም ወጣቶች

መዝሙር ነውን? የሚል ጥያቄ በማንሳት ብዕሬን ከወረቀት ጋር አገናኝቻለሁ፡፡ እርግጥ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች የእምነት ነፃነታቸው ተገፎ ከሆነ፤ ተቃውሞ ማንሳት የሚጠበቅባቸው ሙስሊም ወጣቶች ብቻ ናቸውን?—ተከታዩ ጥያቄዬ ነው።

እኔ በግሌ ፀሃፊው በኢትዮጵያ ሙስሊም ወጣቶች ተከልለው እንደ ፈሪ ልጅ ድንጋይ ለመወርወር ዳዳቸው እንጅ፤ በተጨባጭ እርሳቸው "ዘማሪ ወጣቶች" ያሏቸው ሙስሊሞች የሉም፤ እንዲያውም ለድርሰታቸው የፈጠሯቸው ቅዥት ወለድ ፍጡራን ናቸው፡፡

አቶ ኃይለመስቀል ክርስቲያን ጓደኞቹ እንደሚሉት "እንደ ጲላጦስ ከደሙ ንፁህ ነኝ" ለማለት የፈለጉ ብልጣብልጥ ብዕረኛም ይመስላሉ— ከፅሁፋቸው እንደምገነዘበው። ምክንያቱም ሆን ብለው እንደሆነ ርግጠኛ ባልሆንም፣ የሙስሊሙን ህብረተሰብና መንግስትን ለማላተም ማቀዳቸውን የዘገባቸው ፋካሬያዊ ፍቺ በግልፅ የሚያስረዳ ስለሆነ ነው። እናም በትንሽዬ ብልጣብልጥነት ሚዛናዊ ፍርድ የአንባቢው መሆኑን ለማስመሰል ሞክረዋል፡፡ እኔም "የማን አባት ገደል ገባ?" የምትል አሮጌ ተረታቸውን በመታዘቤ ነው፤ የክርስቲያኖችን "ጲላጦሳዊነት"ን እንደተመኙ የገመትኩት፡፡

በእስልምና ስም በመሸጉ ጥቂት አክራሪ ፖለቲከኞችና በነባሩ የኢትዮጵያ ሙስሊም መካከል የተፈጠረው አለመግባባት እንዴት እንደተፀነሰ፤ ተባብሶም ሃገራዊ ሥጋት እንደሆነና መንግስትም እንደምን ችግሩን ለመቆጣጠር የራሱን ርምጃ እንደወሰደ ለማመልከት ሞክረዋል— በመግቢያው የማጫጫሂያ ክፍል፡፡ የፅሑፋቸው ዋና ክፍልና ድምር ጭብጡ ግን መንግስት በኃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ እየገባ መሆኑን ያስተምራል፤ ሙስሊም ወጣቶች ለፀረ-መንግስት /ለፀረ-ሀገር/ ትግል እንደተዘጋጁም ያውጃል፡፡

እርግጥ ፀሃፊው የዛሬ ዓመት ገደማ ተፈጥሮ የነበረውን የአክራሪዎችን የሁከት እሰጥ- አገባ ለማሳየት መሞከራቸው ክፋት የለውም፡፡ ክፋቱ ግን ግለሰቡ ከመነሻው ጀምሮ የነበረውን ሂደት ለመላ አንባቢው በማቅረብ ፍርዱን ለታዳሚው ለመተው ከመፈለግ የመነጨ አለመሆኑ ነው። ከዚህ ይልቅ ትልቁ ፍላጎታቸው በብልሃት የመንግስትን "ጣልቃ ገብነት" ማራገብ ነው፡፡

እናም ግለሰቡ በፅሑፋቸው የሰጡን መረጃ "አንዱን ጥሎ አንዱን አንጠልጥሎ" የሚሉት ዓይነትና ሚዛናዊነት የጐደለው ነው፡፡ ምክንያቱም በሙሉ ፅሁፋቸው መንግስት የሙስሊሙን ህብረተሰብ ከእምነቱ እያስተጓጐለው ነው ከማለት በስተቀር፤ ዋናውን ጉዳይ የዋህቢያን ምንነት፣ በኢትዮጵያና በአፍሪካ፣ በመካከለኛው ምሥራቅና በመላ ዓለም እየደረሰ ያለውን ጥፋት ሊነግሩን ስላልፈቀዱ ነው። ዓላማቸው ሃቁን በመደበቅ የግል ጥቅማቸውን ማጧጧፍ ላይ ያተኮረ ነው፡፡

ፀሐፊ ተብዬው ሃቁን ተረድተን የራሳችን ሚዛናዊ ፍርድ እንድንሰጥ ዕድል ነፍገውናል፡፡ በእርግጥ እርሳቸው የደበቁን የደባባይ ምስጢር በመሆኑ የቀረብን ነገር ያለ አይመስለኝም፤ ደግሞም የእርሳቸው ዓላማ የሙሥሊሙ ህብረተሰብ የእምነት ነፃነቱ እየተገፈፈ መሆኑን በማራገብ፣ መንግሥት ላይ ነፍጥ እንዲያነሣ መታተር በመሆኑ እውነታውን ባይነግሩን አይገርመንም፡፡

ግለሰቡ የተጠቀሙባቸውን ቃላት፣ ሃረጋትና አንቀፆች በቀጥታ ወይም እንደ ወረዱ በመምዘዝ የጥፋት አጫዋችነታቸውን መመልከት ይቻላል፡፡ እርሳው እንደሚሉት በሽብር ተግባር ተጠርጥሮ ቁጥጥር ስር የዋለው አክራሪ ኮሚቴ ተመራጭነት በህዝበ ሙስሊሙ እየሰፋ ሲሄድ፣ መንግሥት ኃይማኖታዊ መንግሥት ከመመሥረት ጋር አያይዞ ብዙዎችን የኮሚቴ አባላት በአሸባሪነት በመክሰስ ጥያቄውን እንዳዳፈነ ደምድመዋል-የጨለማው ዘማሪ ፀሐፊ ተብዬ፡፡

እንግዲህ ልብ በሉ! በመጀመሪያ ደረጃ ግለሰቦችን በህግ ተጠያቂ ማድረግና በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ መግባት በየትኛው ሂሳባዊ ቀመር እንደሚጣመሩ ለ15 ቀኑ አደናቋሪ ካልሆነ በስተቀር ለማንም ግልፅ አይደለም፡፡ ማንኛውም የዚህ ፅሑፍ አንባቢ እንደሚያውቀው ግለሰቦቹ በአሸባሪነት ተጠርጥረው እንጂ ሙስሊም ስለሆኑ አይደለም ክስ የተመሰረተባቸው። እናም መንግሥት የእምነቱን ተከታዬች አሊያም ተመራጮችን ተጠያቂ ማድረጉ በእምነቱ ጣልቃ እየገባ ተደርጐ መወሰዱ ተቀባይነት የሌለው ጉዳይ ነው፡፡

በእርግጥ ፀሃፊው እንደዚያ ቢገምቱ፣ ወይም ሃቁን እያወቁት ያልተገባ አካሄድ በመቀመር አንዳንድ ተላላ ፍጡራን ከተገኙ ለማወናበድ መባጀታቸው አያስገርምም፡፡ ሰው መቼም እንደዚያ ለምን ገመትክ ተብሎ አይወቀስም፡፡ ምንም እንኳን በማይመለከተንና እውነታውን በማናውቀው ጉዳይ እየገባን ባለማወቅም ይሁን ሆን ብለን በድፍረት መፈትፈት ቢያያንስ የህሊናም ተጠያቂ ከመሆን አያድንም። ግለሰቡ እንደዚያ ገምተዋል ብሎ መገመት ግን የዋህነት ነው። ምክንያቱም የሚፅፉበት መፅሔት የጥፋት ዘዴ የሚከተል በመሆኑ ነው፡፡

ያም ሆነ ይህ አቶ ኃይለ መስቀል አንድ ሃቅ የዘነጉ ይመስለኛል፡፡ ምናልባት እርደሳቸው የእምነቱ /እሥልምና/ ተከታይ ባለመሆናቸው ጉዳዩን በቅርበት አያውቁት ይሆናል፡፡ ባለማወቃቸው ግን የዘበዘቡልን ፍሬ አልባ ጽሑፍ እንደዘበት መታለፍ ያለበት አይመስለኝም፡፡ ምክንያቱም ፊደል ቆጥሬያለሁ ለሚል ሰው አለማወቅ ከተጠያቂነት ሊያድን ስለማይችል ነው። የማያውቁትን ነገር በድፍረት መፃፍ በጋዜጠኝነት የሙያ ስነ-ምግባርም ቢሆን አግባብነት የሌለው አሰራር በመሆኑ ነው፡፡

እርሳቸው የማናውቀውን መረጃ ሊሰጡን የፈለጉ ፀሃፊ መስለው ያስነበቡን ረጅም ድርሰት መሰል ጽሁፍ መሠረተ-ቢስ መሆኑን የምናውቀው እኛ ነን– የእምነቱ ተከታዮች፡፡ ለምን ቢሉ፤

ከፀሐፊው ይልቅ እኛ የእምነቱ ተከታዬች ጉዳዮን በቅርበት ስለምናውቀው ነው–ሀገራዊ ብሂላችንም “ማን ያርዳ የቀበረ፣ ማን ይናገር የነበረ” ይላልና፡፡ እናም ሰውዬው ይልቅ እኛ ሙስሊሞች ስለ ጉዳዩ ብንናገር የሚያምርብን ይመስለኛል፡፡ በመሆኑም ለጨለማው ዘማሪ “ ድብቅ የተልዕኮ ፖለቲካዊ ሴራዎን ለመጠንሰስ ሲሉ በስማችን ከመነገድ ይቆጠቡ” የሚል ግላዊ መልዕክቴን ልነግራቸው እወዳለሁ።

አቶ ኃይለ መስቀል መንግሥት በአሸባሪነት የከሰሳቸው ግለሰቦች ተበዳዮች እንደሆኑ አድርገው ደምድመዋል። ግና ሃቁን ዘንግተውት አይመስለኝም፡፡ የፀሃፊውን አገላለጽ ቃል በቃል ልዋስና “… ብዙዎቹን የኮሚቴውን አባላት በአሸባሪነት በመክሰስ ጥያቄውን ለማዳፈን ሞከረ…. “ይላሉ እኚሁ የቀበሮ ባህታዊው “የሙስሊም ጠበቃ”፡፡

እንደ እርሳቸው አገላለጽ፤ የታፈነው ወይም ለመዳፈን የተሞከረው የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ጥያቄ ነው፡፡ መቼም አጃኢብ ነው። መነጋገር ካለብን ጉዳዩን በግልጽ አፍረጥርጠን ማውጋት ይኖርብናል፡፡ ሁላችንም እንደምናውቀው መንግሥት በአሸባሪነት በመጠርጠር ከስሶ ለህግ ያስተላለፋቸው ግለሰቦች የኢትዮጵያ ሙስሊሞችን የሚወክሉ እንደራሴዎች አድርጐ እያቀረቡ አቧራ ለማስነሳት መጣጣር ተገቢ አይመስለኝም፡፡

ሰውዬው መንግሥት የሙስሊሙን ተወካዮች ያፈነ አስመስለው ነገሩን እንጂ ሙስሊሙ ህብረተሰብ ግለሰቦቹን መቼና የት እንደወከላቸው እንኳን የሚያውቁት ቅንጣት ነገር የለም፡፡ ግና በመሠረቱ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች መንግሥት ነበሩን እስልምና ለማፍረስ ሲዳክሩ የነበሩ የፖለቲካ ሴረኞችን /ፀሐፊው የሙስሊሙ ተመራጭ ብለው የገለጿቸው/ አደብ ለማስገዛት መዘግየቱ፣ ህግና ሥርዓትን ከማስፈን አኳያ ትዕግስትን አብዝቶት እንደነበር የምናስታውሰው ሃቅ ነው፡፡

ታዲያ ግለሰቡ መንግሥት በእስልምና ኃይማኖት ጣልቃ እንደገባ አድርገው በመቁጠር ህዝበ- ሙስሊሙንና መንግሥትን ለማላተም የሚጣደፉት ይህ ዕውነታ ባለበት መሆኑን መገንዘብ ያሻል፡፡ እርግጥ ሁሌም ቢሆን መንግስት ማንኛውም ዜጋ የሚያነሳውን ጥያቄ የሚመለከተው ጉዳዩን በመመርመር በቅን ልቦና ነው። ሁኔታው ሲመረመርም ኢትዩጵያ ውስጥ ያለው ችግር የሃይማኖት ጥያቄ ሳይሆን የፖለቲካ አክራሪነትና የአሸባሪነት ጉዳይ ነው። በቅርቡ ከፍርድ ቤቶች የወጡት ብይኖችም የሚያመላክቱትም ይህንኑ ነው።

መንግስት በማስረጃ ላይ ተመስርቶ ማንኛውንም የሽብር ሃይል ተቆጣጥሮ የሚይዝበት የተደራጀ ሃይል ያለው መሆኑም ሊዘነጋ አይገባም። ይህን አካሄዱን ሲከውንም ስንዴውን ከእንክርዳዱ በሚለይ ሁኔታ ነው– ጥቂት አሸባሪ ተጠርጣሪዎችን ከአብዛኛው ንፁህ ሙስሊም በሚያንጓልል መልኩ።

እናም ሊበታትኑንና ነባሩን እስልም ብሎም ከቀሪው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ሊያባሉት የነበሩ ግለሰቦች ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ፣ ሀገራችን ተቻችለን በአንድነትና በመተሳሰብ የምንኖርባት ምድር እንድትሆን መንግሥት እርምጃ መወሰዱ ተገቢ መሆኑ አያጠያቅም፡፡ በመሆኑም እርሳቸው እንደሚነግሩን መንግሥት የሙስሊሙን ጥያቄ የሚባለው ሰበባ ሰበብ አፈ-ታሪክ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ፀሐፊው ከምን ተነስተው ግለሰቦቹን ከወንጀል የፀዱ አድርገው እንደመሰከሩላቸው ለማንም ግልፅ አይደለም፡፡ ሰዎችን በዓይን ተመልክተው ነፃና ወንጀለኛ መሆናቸውን መለየት የሚያስችል ቴክኖሎጅ አሊያም በነብይነት ተቀብተው ካልሆነ በስተቀር፤ በምንም ዓይነት መስፈርት ቢመዘን አቶ ኃይለመስቀል መንግሥት ተጠርጣሪዎቹን ለማፈን ፍላጐት እንዳለው አድርገው በማስመለስ ወሬ መፈብረካቸው ግጭት ለመፍጠር ብቻ መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው ፡፡

ተጠርጣሪዎቹ ነፃ አሊያም ወንጀለኛ መሆናቸው ገና ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ህግ የያዘውን ጉዳይ በማንሳት ያልተገባ ትርጉም ለማሠጠት መሞከር ተጠያቂም የሚያደርግ ነው። እናም እንዲህ ዓይነቱ የጭፍን ጉዞ ብልሃት እንዳልሆነ ፀሃፊው ይዘነጉታል ብዬ አልገምትም፡፡ ሰዎችን ነፃ የመልቀቅም ይሁን ፍርድ የመስጠት የፍትሕ አካላት እንጂ በስሜት እየተነዱ በሚሰጥ ተራ አሉባልታ አይደለምና፡፡

እርግጥ እኔም ቢሆን ግለሰቦቹ ወንጀለኞች ናቸው እያልኩ አይደለም፡፡ ነፃም ናቸው አላልኩም፡፡ ያንን ማድረግ የሚችለው ህግ እንጅ እኔ ስላልሆንኩ በማያገባኝና በማላውቀው ጉዳይ እየገባሁ እንደ ፀሐፊ ተብዬው መፈትፈት አልፈልግም፡፡ ግና በአንድ ጉዳይ ላይ መተማመን እንችላለን– ከአቶ ተመስገን አጀንዳ ፀሃፊው ጋር፡፡

እንደሚታወቀው መንግሥት ግለሰቦቹን በአሸባሪነት ጠርጥሮ ለህግ ያቀረባቸው ያለ ምክንያት አይደለም፡፡ ሙስሊሞች ስለሆኑም አይደለም፡፡ ምክንያቱም መንግሥት በአሸባሪነት ጠርጥሮ የከሠሳቸው ተጠርጣሪዎች ፀሃፊው እንደሚሉት የሙስሊም እምነት ብቻ ሣይሆን የሌላ እምነት ተከታዮችንና ከሌላ ሀገር ለግብረ-ሽበራ ተግባርን ለመምራት የሀገራችንን ድንበር ጥሰው የሚገቡ የሌላ ሀገር ዜጎችን ጭምርም ነው፡፡ ለዚህም በቅርቡ ፍርድ ቤት ቀርቦ የሽብር ተግባርን ለመምራት ስልጠና ሊሰጥ ሲዘጋጅ የነበረው፣ ራሱም ይህን ክንዋኔ ለመፈፀም ሲዘጋጅ እጅ ከፍንጅ በቁጥጥር ስር መዋሉን ያመነውና የኬንያ ዜግነት ያለው ሃሰን ጃርሶ የተባለው የአል-ቃዒዳ ክንፍ አባልን መጥቀስ ይቻላል።

እናም በአንድ ነገር እርግጠኛ መሆን ይቻላል፡፡ ይኸውም ግለሰቦቹ በአሸባሪነት የተከሰሱት ሙስሊሞች ስለሆኑ አለመሆኑን ነው፡፡ መንግሥትም የህዝበ ሙስሊሙን የእምነት ነፃነት እየገደበ

እንዳይደለ መመስከር እችላለሁ። ምክንያቱም እኛ ሙስሊሞች የጨለማው ፀሐፊ ለፖለቲካ ፍጆታቸው ሲሉ ብቻ እንደ ደሰኮሩት ሳይሆን፤ በአዲሲቷ ኢትዮጵያ ከመቼውም ጊዜ በላይ እምነታችንን በነፃነት እንድናካሂድና በርካታ መስጊዶችንም እንድንገነባ ተፈቅዶልናል፡፡ ከዚህ ባለፈም መንግሥት በእምነት ጉዳይ ጣልቃ ልግባ ቢልም መብት የለውም– ህገ-መንግሥቱ ይከለክለዋልና፡፡ እናም ፖለቲከኛው ፀሐፊ እየመረራቸውም ቢሆን ይህን ዕውነታ መቀበል ይኖርባቸዋል።

ይህ ማለት ግን ህዝበ- ሙስሊሙን እርስ በርስ ለማባላት የተዘጋጁ፣ ከፍ ሲልም ሃገሪቱን የሚያፈርስና ህገ-መንግሥታዊ ሥርዓቱን የሚንድ ደም አፋሳሽ የሆነ መጤ እምነት /ዋህቢያ/ ትውልድን ለጥፋት ሲያጠምቀው መንግስት እጁን አጣጥፎ ይቀመጣል ማለት አይደለም፡፡ እንዳሻው ጣልቃ የመግባት መብት የሌለውን ያህል፤ ችግሮች ሲከሰቱ መፍትሔ የማፈላለግ መብትም ሆነ ግዴታም እንዳለበት ለሁላችንም ግልጽ ነው፡፡ እናም መንግሥት ህገ-መንግስታዊ ተልእኮውን ለመፈፀም አሸባሪዎችን ለህግ ማቅረብ ከሃይማኖት ጣልቃ መግባት ጋር ተዛምዶ መነገሩ የሚያስተዛዝብ አለባልታ ነው፡፡

በመሠረቱ እውነቱን እንነጋገር ከተባለ የኢትዮጵያ እስልምና የታፈነበት፣ የኢትዮጵያ ሙስሊሞችም ሃይማኖታዊ ሥርዓቱን በነፃነት ለማከናወን ዕድሉን የተነፈገበት ዘመን ካከተመ እነሆ 21 ዓመታትን አልፏል፡፡ ምናልባት ፀሐፊ ተብዬ ያንን ዘመን ቢበዛ በስሚ ስሚ እንጂ በተግባር ስለማያውቁት አይፈረድባቸውም፡፡ በእርግጥ ዛሬም ቢሆን እምነቱና የእምነቱ ተከታዮች ተበዳይ እንዳልሆኑ ጠፍቷቸው አይደለም– አውቀው ስለተኙ እንጂ፡፡

እኔ በበኩሌ መነግስት ግለሰቦችን የህግ ተጠያቂ ማድረጉ ሰውዬውን እንደምን እንዳስጨነቃቸው ሊገባኝ አልቻለም ፡፡ እኔም፣ መላው ሙስሊምም ሆንን ምናልባትም ፀሃፊውም ጭምር ቢሆኑ እንደሚያውቁት፤ ጭፍን አክራሪዎች የሙስሊሙን ህብረተሰብና የሀገራችንን ልማታዊና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማመስ ቆርጠው መነሳታቸውን ይዘነጉታል ብዬ አላስብም። ምናልባትም አይበለውና እንዲህ ዓይነት ቀውስ ሀገራችን ውስጥ ቢፈጠር ሌላው ቀርቶ በጨለማው ውስጥ እየተውረገረጉ ወረቀትና ብዕር ተገኘ ተብሎ የመለቅለቅ ዕድሉም ሊኖር እንደማይችል መገንዘብ ያባት ይመስለኛል።

ግና ነገሩ "ሣይቃጠል በቅጠል" እንዲሉት ሆኖ፤ ሰላም ወዳዱ ህዝበ-ሙስሊምና መንግሥት እጅና ጓንት ሆነው እነዚያን እፍኝ የማይሞሉ አክራሪዎችን መቆጣጠር ተቻለ እንጂ፤ እንደ ጅማሪያቸው ቢሆን ኖሮ ዛሬ ሀገራችን የግጭት አውድማ እኛም ተረት ሆነን በቀረን ነበር፡፡ እርግጥ ምን እያልኩ እንደሆነ አቶ ሃይለመስቀል ይገባቸዋል ብዬ አስባለሁ። አዎ! በእርግጥም ለእርሳቸውና "ለትግል አጋሮቻቸው" በግልፅ እየነገርኳቸው ያለሁት ዕውነታ ሀገርን የማበጣበጥና

ወጣቶችን ወደ ጥፋት ጎዳና የመምራት ህቡዕ ሴራችሁ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ እንዲህ ዓይነቱን ተግባር ማበረታታት ግን ወላፈኑ መልሶ ራስን ሊቃጥል እንደሚችል በሰከረ ሳይሆን በሰከነ አዕምሮ ማመዛዘን እንደሚያሻ ነው።

እኔ በግሌ መንግሥት ከፅንፈኛው የዋህቢያ ደም አፋሣሽ የፖለቲካ አመፀኝነት ስለታደገን መመስገን ያለበት አለበት እላለሁ— በጭፍን የፖለቲካ አሉባልታ መወቀሱ ቀርቶ፡፡ በእርግጥ አቶ ኃይለመስቀልና እንጅ ህዝበ- ሙስሊሙ መንግሥት የወሰደውን እጦፊዎችን ወደ ህግ የማቅረብ እርምጃን በደስታና በፀጋ እንደተቀበለው ይታወቃል፡፡

ማንኛውም የዚህ ፅሑፍ አቅራቢ እንደሚያውቀው ዋህቢያ የራሳቸው ፍላጎት ካላቸው አንዳንድ ሃገራት በሚጐርፍለት ድጋፍ እየተጋዘ በእርዳታና በሃይማኖታዊ ተግባራት ሥም የሚንቀሳቀስ አክራሪም ድርጅት ነው፡፡ ይህን ፀሃፊውም ገልፀውታል— ምንም እንኳን ድብቅ አጀንዳቸውን የሚያሳብቅባቸው ስለመሰላቸው የቡድኑን /የዋህቢያ/ ባህሪ አፍረጥርጠው ሊነግሩን ባይፈልጉም። ታዲያ እዚህ ላይ ሰውዬው በአክራሪዎች ምክንያት በናይጀሪያና በማሊ እንደ በግ የታረዱ ሙስሊሞችን ጉዳይ እንደምን እንዳድበሰበሱት ሳስበው እውነተኛው የሽብር አጋፋሪ መሆናቸውን ለመገመት አላዳገተኝም።

እርግጥ የዋህቢያ ዋነኛው ፍልስፍና አሸባሪነትን መስበክ ነው – በግልፅ ቋንቋ፡፡ ጨዋታው ሁሉ የነባሩን እስልምና ተከታዬች አንገት መቅላት ብሎም የቱሪስት መስህብ የሆኑ ቤተ-መስጊዶችንና ከዕምነቱ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ታሪካዊ ቦታዎችን ማፍረስ እንዲሁም የሃይማኖቱን ሊቃውንቶች መግደል ነው። የመጨረሻ ግቡም በኢትዮጵያ ኢስላማዊ መንግሥት ማቋቋም ነው፡፡

የዋህቢያ እኩይ ምግባር በዚህ ብቻ የሚያበቃ አይደለም፡፡ ኢስላማዊ መንግሥት በኢትዮጵያ አቋቁሞ የብዛሃነት ተምሣሌት የሆነችውን ሃገራችንን የፍልስፍናው ማዕከል ማድረግ በእጅጉ ይፈልጋል። ግና ምን ያደርጋል?!… እንዲህ ዓይነቱ የጠባቦች አመለካከት በአዲሲቷ ኢትዮጵያ ውስጥ ገቢራዊ ማድረግ ግመልን በመርፌ ቀዳዳ ውስጥ የማሽሎክ ያህል በመሆኑ የሚቻል አይደለም።

ለነገሩ ዋህቢያና ዋህቢያ ያሰለጠናቸው ጥቂት ግለሰቦች በኢትዮጵያ ሙስሊሞች ላይ የደረሱትን ጉዳት የምናውቀው እኛ ሙስሊሞች ነን። ዛሬ በዘገባቸው የወንጀል ተጠርጣሪዎች አንቆለጳጳሽ ሆነው የቀረቡት ፀሃፊው ግን ፊደላዊ ሆነው በነሲብ “እገሌ እንዲህ አለ” እያሉ ከመለቅለቅ በስተቀር ስለ ጉዳዩ የሚያውቁት ነገር የላቸውም። ለምን ቢሉ ጉዳዩ “የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሣም” ነውና በጠራራ ፀሃይ የተወገዙ፣ የተገረፉና የታረዱ የእስልምና ተከታዩችን እኛ ሙስሊሞች ልንረሳቸው ስለማንችል ነው።

ሌላው ቀርቶ ዋህቢያ ላይ ዘግናኝ ድርጊቶችን ፈፅሟል፡፡ ሙስሊሞችን በአደባባይ አርዷል፡፡ የነባሩን እስልምና ኢማሞችንና ተከታዬችን አንገላትቷል፡፡ ቤተ-እምነቶችን አፍርሷል፡፡ ኃይማኖታዊ ቅርሶችና አቃጥሏል፤ ዘርፏል፡፡ ከሁሉም የሚከፋው ደግሞ የሙስሊም እምነት ተከታዩችን መቃብር በመቆፈር በክብር ያረፉ አፅሞችን እያወጣ ለጅብ ሰጥቷል፡፡ ይህ ብቻ አይደለም። የመረዳዳት ባህላችንን ሣይቀር የሚቃወምና በተግባርም የሙስሊም በጐ አድራጐት ተቋማትን ያወገዘ፣ እንዲዘጉ ያደረገና የተቋማቱን ሠራተኞች ያዋረደ ፅንፈኛ ድርጅት ነው፡፡

እንግዲህ የፀሃፊው ክፋት በዋነኝነት የሚመነጨው ከዚህ ነው፡፡ ግለሰቡ ይህን እኩይ የዋህቢያ ባህሪ ሊነግሩን አልፈቀዱም፡፡ እኛ ሙስሊሞች እውነታውን ማወቃችን በጀን እንጅ፡፡ ታዲያ መንግሥት ለህግ ያቀረባቸው ከእነዚህ የጥፋት ሃይሎች ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ንክኪነት ያላቸውን የዋህቢያ አጋሮችንና ሸሪኮችን ነው፡፡ እናም ፀሃፊው ለእምነቱ የቆሙ ግለሰቦችን በማሰር ጣልቃ ገብነቱን አጧጡፎታል ሲሉ መንግሥትን ለማብጠልጠል ቢሞክሩም ሃቁ ይኸው ነው፡፡

እናም አቶ ኃይለመስቀል እንደሚሉት መንግሥት በአሸባሪነት ጠርጥሮ ለህግ ያቀረባቸው ግለሰቦች ከሃይማኖቱ ጋር ንክኪ ያላቸው አይደሉም። አብዛኛውን ህዝበ-ሙስሊም የሚወለውን ነባሩን እስልምና የሚወክሉ ሣይሆኑ፤ ከባህር ማዶ በሚላክላቸው ረብጣ ዶላር እየተገዙ አሸባሪነትን በመስበክ በተጨባጭ ደም ያፈሰሱ የዋህቢያ ተላላኪዎች ናቸው፡፡ ግለሰቦቹ ኃይማኖታዊ መንግሥት በመመሥረትና የሰለፍያን ኢስላማዊ ዘውግ በማስፋፋት ሃገራችን የቦኮ ሃራምና የአል-ቃኢዳ ህዋሶች መፈልፈያ እንድትሆን ለማድረግ ሲሰሩ የነበሩ ተጠርጣሪዎች ናቸው፡፡

ምናልባት ስለ ግለሰቡ /ስለ ፀሃፊው/ እርግጠኛ መሆን ባይቻልም በማሊና በናይጀሪያ የምናስተውለው ፅንፈኝነትና ደም አፋሳሽነት በሀገራችን እንዲስፋፋ የሚፈልጉ ያስመስልባቸዋል፡፡ ግና ለጊዜያዊ ጥቅም እስካልተገዙ ድረስ ኢትዮጵያዊ በመሆናቸው እርስ በእርሣችን እንደ እፍኝት ተበላልተን እንድንጠፋፋ የሚቋምጥ ልቦና ይኖራቸዋል ብሎ ማሰብም ይከብዳል፡፡ ሆኖም የብዕራቸው ጠቋሚ ምልክት የሚያሳየን አጋጣሚውን ተጠቅመው በሚያገኙት ቀዳዳ የህዝበ-ሙስሊሙንና የመንግሥትን አንድነት ለማናጋት መፈለጋቸውን ነው፡፡

አቶ ኃይለመሥቀል በሸዋምየለህ ፅሁፋቸውን የደመደሙት በሆነች ትንቢት ቢጤ መልዕክት ነው፡፡ መቸም ለልጅ ይታየዋል አይደል። የሆነ አንዳች አደገኛ ነገር በቅርቡ እንደሚፈነዳ የሚያውቁ ይመስላሉ፡፡ በእርግጥ ለእርሳቸው መልካም ምኞትም ይመስላል፡፡ ለእኛ ግን ቀጭን የክተት ጥሪ ነው፡፡ "አሽ ሸዓብ ዮሪድ ተቀይሩል መጅሊስ" ብለው በቀመሩት ንዑስ ርእስ ለኢትዮጵያ ሙስሊም ወጣቶች ቀጭን የክተት ጥሪ ጣል አድርገዋል፡፡

ፀሐፊው ስለየትኛው ወጣት እንደሚነግሩኝ ባላውቅም፤ ወጣቶች እየዘመሩ ነው። እናም ”አሽ ሽዓብ ዩሪድ ተቀይሩል መጅሊስ” ይላሉ፡፡ መዝሙሩን እነማንና የት እየዘመሩት እንደሆነ አላውቅም። ለነገሩ ፀሃፊው በቅዠት ካልሆነ በስተቀር የሚያውቁት አይመስለኝም፡፡  ሆኖም እንዲያው ሆዴ ሲጠረጥር ግን ነገሯ በሆነ አንድ የአረብ ሀገር መንደር ውስጥ ያሉ ወጣቶች የሚዘምሯት መንዙማ ትመስለኛለች፡፡

ወጣም ወረደ ግን ፀሃፊው ሊነግሩን የፈለጉት ወጣቱ ለእምነቱ ሊሞት እንደተዘጋጀና ሰውነቱን እያሟሟቀ በመጠባበቅ ላይ እንዳለ ነው። ወይም ህዝበ-ሙስሊሙን ሊያስፈራሩት ሞክረዋል፡፡ ታዲያ እኛ እንደምን አንፈራ?፣ መተላለቅ ያላስፈራንስ ሌላ ምን ያስፈራናል?... ደግነቱ ዛሬ የሚነገረውን ሳይሆን የሚያየውን የሚያምን ትውልድ እንጂ ወደ መሩት የሚፈስ የሜዳ ውሃ አይነት ሙስሊም የለም፡፡ ሃቁ፤ መሬት ላይ ያለውን እውነታ የምናውቀው እኛ ሙስሊሞች ነን፡፡

ሙስሊሙ ህብረተሰብ የሚበጀውን በጆሮው ሳይሆን በአይኑ አይቷል፡፡ በተግባር አይተናል፡፡ እናም ጥቂት በዶላር የተገዙ የዋህቢያ አገልጋዬችና አጋጣሚውን በመጠቀም የፖለቲካ አጀንዳቸውን ለማቀጣጠል ነዳጅ የሚረጩ እንደ አቶ ሃይለመስቀል ዓይነት  የእኩይ ምግባር ተንታኞች አይፈታንም፡፡ እናም “ለእምነቱ የቆሙ ሙስሊሞች ታሠሩ፣ መንግሥት የእሥልምና ተከታዮችን የእምነት ነፃነት ነፍጓል” የሚለው በሙስሊሙ ስም የተሰናዳው የፖለቲካ ጨዋታ መሠረተ- ቢስ መሆኑን ማወቅ ይበጃል ባይ ነኝ፡፡